# ለ COVID-19 ምልክቶች በየቀኑ ዕለታዊ ምርመራ በቤት ውስጥ

***ይህ የመመርመሪያ መሳሪያ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎች እና ለማንኛውም የቤተሰብ አባል ነው።***

**ክፍል 1 - ምልክቶች: ከነዚህ ምልክቶች አንዱ አለዎት?**

*በይበልጥ የተለመዱ ምልክቶች*

- ❏ 100.4 ዲግሪ ፋራናይት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ትኩሳት ካለብዎ (እባክዎ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄድዎ በፊት በየቀኑ የሙቀት መጠንዎን ይለኩ)
- ❏ አዲስ የጀመረዎት/ብቅ ያለ ሳል ወይም የከፋ ሳል
- ❏ ለመተንፈስ መቸገር
- ❏ አዲስ ጣዕም ወይም ሽታ መጥፋት

*በመጠኑ የተለመዱ ምልክቶች*

- ❏ የጉሮሮ መቁሰል
- ❏ ማቅለሽለሽ
- ❏ ማስታወክ
- ❏ ተቅማጥ
- ❏ የብርድ ስሜት
- ❏ የጡንቻ ህመም
- ❏ ከመጠን በላይ ድካም
- ❏ አዲስ ወይም ከባድ ራስ ምታት
- ❏ አዲስ የጀመረዎት/የአፍንጫ መዘጋት ወይም የአፍንጫ ፍሳሽ

**ክፍል 2 - ለቅርብ ሰው ተጋላጭነት**

**የቅርብ ግንኙነት በስድስት ጫማ ወይም ከዚያ ለሚቀርብ ርቀት ለ 15 ደቂቃ ወይም ከዚያ ለሚበልጥ ጊዜ ተብሎ ይገለጻል።**

- ❏ በCOVID-19 መያዙ ከተረጋገጠ ሰው ጋር በቅርብ ተገናኝተዋልን?
- ❏ እርስዎ ወይም የበሽታው ምልክት ያለው ሌላ ማንኛውም የቤተሰብ አባል (ከ COVID-19 ጋር የሚዛመዱ ምልክቶች ያለው ሰው) በአሁኑ ጊዜ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቶችን በመጠባበቅ ላይ ነው?
- ❏ ከህዝብ ጤና ጥበቃ ባለሥልጣን ወይም ከሕክምና ባለሥልጣን እራስዎን ለይተው ማቆየት እንዳለብዎ ተነግሮዎታል?

**ክፍል 3 - ቀጣይ ደረጃዎች**

**ቤት ውስጥ መቆየት ያስፈልገኛል?**

- ❏ **ከላይ በክፍል 1 ውስጥ** አንድ ወይም ከዚያ በላይ **በይበልጥ የተለመዱ ምልክቶች (ትኩሳት ፣ ሳል...) ካለዎት፣ ቤትዎ ይቆዩ።** የቤተሰብ አባላትም ቤታቸው መቆየት አለባቸው።
- ❏ **በመጠኑ የተለመዱ** ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ **ምልክቶች (የጉሮሮ መቁሰል፣ ማቅለሽለሽ...) ካለዎት ቤትዎ ይቆዩ ።** የቤተሰብ አባላትም ቤታቸው መቆየት አለባቸው።
- ❏ **በክፍል 2 ውስጥ** ላለ ማንኛውም ጥያቄ **አዎ** የሚል መልስ ከሰጡ በቤትዎ ይቆዩ።

**ወደ ማን ልደውል?**

- ❏ ተማሪዎች መቅረታቸውን ሪፖርት ለማድረግ ወደ ትምህርት ቤታቸው መደወል አለባቸው።
- ❏ ሰራተኞች ለርእሰ መምህራን / ተቆጣጣሪ መደወል አለባቸው; እንዲሁም ምን ዓይነት ሰነድ እንደሚያስፈልግ ለመወሰን ለሰው ኃይል መደወል አለባቸው።
- ❏ ግምገማ ወይም የ COVID-19 ምርመራ ከፈለጉ ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይደውሉ።
- ❏ MDH COVID-19 የእገዛ መስመር የሕዝብ ጥያቄዎችን በ 651-297-1304 ወይም በ health.covid19@state.mn.us ኢሜል ሊመልስ ይችላል ።

ታደሰ መስከረም 13፣ 2020